የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፵
አዲስ አበባ መጋቢት ፳፯ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No. 40
ADDIS ABABA 5th April, 2018


**ማውጫ**


አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፭/፪ሺ፲ ዓ.ም

የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባና አስተዳደር አዋጅ ..................................................................ገጽ ፲ሺ፫፻፵፰


**Content**


Proclamation No1075/2018

Industrial Chemical Registration and Administration Proclamation……………………………Page 10348


## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፭/፪ሺ፲

## ስለኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባና አስተዳደር የወጣ አዋጅ

ሀገራችን ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ በሽግግር ሂደት ላይ በመሆኗ ከውጪ ሀገር የሚገቡ ወይም በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች መጠን እያደገ በመምጣቱ፤

የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት፣ በማጓጓዝ፣ በማከማቸት፣ በማምረትና በመጠቀም ሂደት ከአያያዝ ጉድለት በሰው፣ በእንስሳት ጤና እና በአካባቢ ደህንነት ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳቶችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ምዝገባና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፭/፪ሺ፲” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 1075/2018

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE REGISTRATION AND ADMINISTRATION OF INDUSTRIAL CHEMICAL

**WHEREAS,** Ethiopia is in the process of economic transformation from agricultural to industrial led economy which in turn steadily increases the demand of imported or domestically produced chemicals;

**WHEREAS**, it is found important to put in place a system to prevent and control of adverse effects to the human and animals health as well as environment safety that may arise from mismanagement of the chemicals in the process of production, importation, exportation, transportation, storage, and use of industrial chemicals;

**NOW THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows.

### PART ONE
### GENERAL PROVISIONS

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the “Industrial Chemical Registration and Administration Proclamation No. 1075/2018”.

## ፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/ "የኢንዱስትሪ ኬሚካል" ማለት ለኢንዱስትሪ፣ ለትምህርት፣ ለሥልጠና ለምርምርና ስርፀት አገልግሎት ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውንም ኬሚካል የሚጨምር ሲሆን የመድሃኒት እና የህክምና፣ የምግብና የምግብ ነክ፣ የግብርና፣ የኬሚካል ጦር መሳሪያዎች እና የጨረር አመንጪ ኬሚካሎችን አይጨምርም፤

፪/ "አካባቢ" ማለት በመሬት፣ በከባቢ አየር፣ በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት፣ በውሃ፣ በህያዋን፣ በድምጽ፣ በሽታ፣ በጣዕም፣ በማህበራዊ ጉዳዮች እና በሥነ ውበት ሳይወሰን፣ በተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች ወይም በሰው አማካኝነት ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በሙሉ ያሉበት ቦታ፣ እንዲሁም መጠናቸው ወይም ሁኔታቸው ወይም ደግሞ የሰው ወይም የሌሎች ህያዋን በጎ ሁኔታን የሚነኩ መስተጋብሮቶቻቸው ድምር ነው፤

፫/ "አግባብነት ያለው አካል" ማለት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲቲዩት፣ የእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና የምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር አስፈፃሚ አካል፣ የንግድ ሚኒስቴር፣ የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴር፣ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ለመመዝገብ ወይም ለማስተዳደር በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች ሥልጣን የተሰጣቸውን አካላት እንዲሁም በክልል ደረጃ የእነዚህን ተቋማት ተግባር የመምራት ሃላፊነት የተሰጣቸውን አካላት ያጠቃልላል፤

፬/ "የምዝገባ ቁጥር" የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን በዓይነታቸው ለመለየትና ጥቅም ላይ ለማዋል የሚሰጥ ቁጥር ነው፤

## 2. Definition

In this Proclamation:

1/ "industrial chemical" means any chemical that is used for industrial, educational and training, research and transfer purposes, with the exclusion of pharmaceutical and medical, food and food additives, agricultural, chemical weapons and radioactive chemicals;

2/ "environment" means the totality of all materials whether in their natural state or modified or changed by humans, their external spaces and the interactions which affect their quality or quantity and the welfare of human or other living things, including but not restricted to, land, atmosphere, weather and climate, water, living things, sound, odour, taste, social factors, and aesthetics;

3/ "competent authority" means includes Ministry of Industry, Chemical and Construction Input Industry Develop ment Institute, Ministry of Agriculture and Natural Resource, Ministry of Health, the Food, Medicine and Health Care Administration and Control Authority, Ministry of Trade, Ministry of Labour and Social Affairs, Ministry of Science and Technology, Ministry of Education, Revenue and Custom Authority, and any governmental institution which has a mandate to register and administer industrial chemicals in according to this Proclamation and other laws, as well as regional responsible entities in charge of these institutions' mandates;

4/ "registration number" means an identification number used to categorize and utilize industrial chemicals;

፭/ "ዳግም ማሸግ" ማለት የኢንዱስትሪ ኬሚካልን ለቀጣይ ሽያጭ እንዲመች ለማድረግ ከአንድ የንግድ እሽግ ወደ ሌላ አብዛኛውን ጊዜ አነስ ወዳለ እሽግ የሚገለበጥበትና እንደገና የሚታሸግበት አሰራር ነው፤

፮/ "ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል ኬሚካል" ማለት የኢንዱስትሪ ኬሚካል ሆኖ፤

ሀ) በስቶክሆልም ወይም በሮተርዳም ስምምነት መሠረት ከአካባቢና ከጤና አንፃር ጥቅም ላይ እንዳይውል የታገደ፤ ወይም

ለ) የአገልግሎት ጊዜው ያበቃ፤ ወይም

ሐ) በአያያዝ ጉድለት የተነሳ የተበላሸ በመሆኑ ምክንያት ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል ነው፤

፯/ "በግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ቅድመ ይሁንታ አሰራር" ማለት በሮተርዳም ስምምነት ውስጥ በዓለም አቀፍ የንግድ ልውውጥ የተወሰኑ አደገኛ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችንና ፀረ-ተባዮችን በተመለከተ ባስቀመጠው መሠረት የታገዱ ወይም በጥብቅ ገደብ የተጣለባቸው ኬሚካሎችና በጣም አደገኛ የሆኑ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ልውውጥና አያያዝ የማሳወቅ አሰራር ነው፤

፰/ "ገደብ የተጣለበት ኬሚካል"ማለት በስቶክሆልም ወይም በሮተርዳም ስምምነት መሠረት ከአካባቢና ከጤና አንፃር ጥብቅ የአጠቃቀም ገደብ የተጣለባቸው እና በግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ቅድመ ይሁንታ አሰራር የሚጠይቁ ኬሚካሎች ናቸው፤

፱/ "የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት በሮተርዳም ስምምነት እና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ ጥብቅ የአጠቃቀም ገደብ የተጣለባቸውን የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ለማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባትና ለመጠቀም የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ካለው አካል የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

5/ "repacking" means the transfer and packing of an industrial chemical from any commercial package into any other, usually smaller container for the subsequent ease of sale;

6/ "obsolete chemicals" means industrial chemical:

a) the use of which has been banned for the environmental or health reasons by applicable provisions of the Stockholm or Rotterdam convention; or

b) that has been expired; or

c) that has been deteriorated as a result of improper management and cannot used again;

7/ "Prior Informed Consent Procedure" means the procedure under the Rotterdam Convention for exchanging and handling information in international trade on banned or severely restricted chemicals and severely hazardous industrial chemicals;

8/ "restricted chemicals" means the use of which has been restricted and oblige to prior informed consent for the environmental or health reasons by applicable provisions of the Stockholm or Rotterdam Convention;

9/ "Certificate of Competence" means a certificate issued by the Ministry or competent authority demonstrating that a person has fulfill the necessary requirements to produce, import and use of industrial chemicals that has been restricted by Rotterdam Convention and directive issued by the Ministry;

፲/ “የሮተርዳም ስምምነት” ማለት በተወሰኑ አደገኛ ኬሚካሎችና ፀረ-ተባዮች የዓለም አቀፍ ንግድን አስመልክቶ በግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ቅድመ ይሁንታ አሰራር ሥርዓት እንዲተገበር በአዋጅ ቁጥር ፪፻፸፰/፲፱፻፺፬ የፀደቀ ዓለም ዓቀፍ ስምምነት ነው፤

፲፩/ “ስቶክሆልም ስምምነት” ማለት ለረዥም ጊዜ ሳይመክኑ የሚቆዩ ከካርበን የተሰሩ በካዮችን በሚመለከት በአዋጅ ቁጥር ፪፻፸፱/፲፱፻፺፬ የፀደቀ ዓለም ዓቀፍ ስምምነት ነው፤

፲፪/ “መለያ” ማለት የተፃፈ፣ የታተመ ወይም በምስል የተቀረፀና በኢንዱስትሪ ኬሚካል ቀጥተኛ መያዣና በቀጥተኛ መያዣዎች ውጫዊ መያዣ ወይም መጠቅለያ ላይ የተደረገ ወይም ከዚህ ጋር የተያያዘ መግለጫ ነው፤

፲፫/ “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደየቅደም ተከተሉ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፲፬/ “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ ፵፯ (፩) የተመለከቱት ክልሎች እና የአዲስ አበባና የድሬደዋ የከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፲፭/ “የኢንዱስትሪ ኬሚካል እንቅስቃሴ” ማለት የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ወደ ውጭ ሀገር መላክ፣ ማሸግ፣ ማጓጓዝ፣ ማከፋፈል፣ ማከማቸት፣ መሸጥ፣ መጠቀም እና ወደ ሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ ነው፤

፲፮/ “አደጋ” ማለት በሰው ወይም በእንስሳት ጤና፣ በአካባቢ ወይም በንብረት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል የኢንዱስትሪ ኬሚካል ተፈጥሯዊ ባህሪይ ነው፤

፲፯/ “መያዥ” ማለት ማንኛውም የኢንዱስትሪ ኬሚካል የተያዘበት፣ የተቀመጠበት፣ የታሸገበት ወይም የተሸፈነበት ሲሆን ከኢንዱስትሪ ኬሚካሉ ጋር ንክኪ ያለውን ማንኛውንም ነገር ይጨምራል፤

10/ “Rotterdam Convention” means the convention on the prior informed consent procedure for certain hazardous and chemicals and pesticides in international trade ratified on July 2002 pursuant to Proclamation No. 278/2002;

11/ “Stockholm Convention” means the convention on persistent organic pollutants ratified on July 2002 pursuant to Proclamation No. 279/2002;

12/ “label” means a written printed or graphic matter on, or attached to the immediate container of an industrial chemical and the outside container or wrapper of the immediate containers;

13/ “Ministry" or "Minister" means the Ministry or Minister of Environment, Forest and Climate Change respectively;

14/ “Region” means any state referred to under Article 47(1) of the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city Administrations;

15/ “industrial chemical transaction” includes manufacturing, importation, exportation, packing, transportation, distribution, storage, selling, using and transferring to third party of industrial chemicals;

16/ hazard” means the inherent property of industrial chemicals or situation having the potential to cause adverse effects or damage to human or animal health, the environment or property;

17/ “container” means anything in which or by which industrial chemicals are encase, covered, enclosed, contained or packed, including materials in contact with the industrial chemicals;

፲፰/ "ማምረት" ማለት የኢንዱስትሪ ኬሚካልን ማሰናዳት፣ ማዋሀድ፣ ማዘጋጀት መቀላቀል ወይም ለማሰራጨት ወይም በጥቅም ላይ ለማዋል እንዲችል ማድረግ ነው፤

፲፱/ "ተጠቃሚ" ማለት የተለያዩ ምርቶችን ለማምረት ወይም ለሌላ አገልግሎት የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን በግብዓትነት የሚጠቀም ማንኛውም ድርጅት ወይም ተቋም ነው፤

፳/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፩/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ያካትታል።

## ፫. የአዋጁ ተፈጻሚነት

ይህ አዋጅ በኢንዱስትሪ ኬሚካሎች እንቅስቃሴ ላይ በሚሰማራ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ፬. የአዋጁ ዓላማ

ይህ አዋጅ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

፩/ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ለመመዝገብ እና ለማስተዳደር የሚያስችል ሀገራዊ ሥርዓት መዘረጋት፤ እና

፪/ ከኢንዱስትሪ ኬሚካሎች እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ በሰው እና በእንስሳት ጤና እንዲሁም በአካባቢ ደህንነት ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳቶችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር።

## ክፍል ሁለት
## የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና ምዝገባ

## ፭. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

በሮተርዳም ስምምነት እና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ ጥብቅ የአጠቃቀም ገደብ የተጣለባቸውን የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት፣ ወደ ውጪ በመላክ እንዲሁም በማከፋፈል ሥራ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ካለው አካል በቅድሚያ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት።

18/ "manufacturing" means to prepare, compound, formulate, mix or make industrial chemicals for its distribution or use;

19/ "user" means any person who use industrial chemicals as an inputs for manufacturing of various products or other services;

20/ "person" means any natural or juridical person;

21/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Scope of Application

This Proclamation shall be applicable to any person who is engaged in the transaction of industrial chemicals.

## 4. Objective

This Proclamation shall have the following objectives:

1/ establishing a national system for registration and administration of industrial chemicals; and

2/ preventing and controlling the adverse effects arising from the mismanagement of chemicals to the human and animals health as well as environment safety that may occur in the transaction of industrial chemicals;

## PART TWO
## CERTIFICATE OF COMPETENCE AND REGISTRATION

## 5. Certificate of Competence

Any person who engages in the importation, exportation, transportation and storage of industrial chemicals that has been restricted by Rotterdam Convention and directive issued by the Ministry shall obtain a certificate of competence from Ministry or competent authority.

**፮. <u>የኢንዱስትሪ ኬሚካል ምዝገባ እና መዝገብ ስለማደራጀት</u>**

፩/ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሀገር ውስጥ የሚመረቱና ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ኬሚካሎችን ዝርዝር እና መረጃ የያዘ መዝገብ ያደረጃል፤ መዝገቡ መያዝ የሚገባቸውን ዝርዝር መረጃዎች በደንብ ይወሰናል።

፪/ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው አካል ያልተመዘገበ የኢንዱስትሪ ኬሚካልን ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ማሸግ፣ መሸጥ፣ ማከፋፈል፣ ማከማቸት ወይም መጠቀም አይችልም።

፫/ አግባብነት ያላቸው አካላት የሚያስተዳድሯቸውን ኬሚካሎች መረጃ በየዓመቱ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መላክ አለባቸው።

፬/ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኬሚካሎችን መረጃ ለሚኒስቴሩ በየዓመቱ ይልካል።

**<u>ክፍል ሦስት</u>**

**<u>መረጃ አያያዝ እና የሪፖርት አቀራረብ</u>**

**፯. <u>መረጃ አያያዝ</u>**

፩/ ማንኛውም የኢንዱስትሪ ኬሚካል የሚያመርት፣ የሚልክ፣ የሚያስመጣ፣ የሚያከፋፍል፣ ወይም የሚጠቀም ሰው የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፦

ሀ) ያመረተውን፣ ወደ ውጭ ሀገር የላከውን፣ ያከፋፈለውን፣ ወደ ሀገር ውስጥ ያስገባውን ወይም የተጠቀመውን የኢንዱስትሪ ኬሚካል ዓይነትና መጠን፤

ለ) በሀገር ውስጥ ገበያ የተሸጠውን እና የተከፋፈለውን የኢንዱስትሪ ኬሚካል ዓይነትና መጠን፤

ሐ) በአያያዝ ጉድለት የተበላሹ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸውን የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ዓይነትና መጠን፤ እና

**6. <u>Registration of Industrial Chemicals and Establishment Registry</u>**

1/ The Ministry of Industry shall maintain an industrial chemicals registry which contains a list and information on industrial chemicals domestically produced and imported from abroad; the details of the information that needs to be maintained in the registry shall be specified by regulation.

2/ No person shall produce, import, pack, sell, distribute, store or use industrial chemicals unless registered by competent authority.

3/ The competent authority shall report information about administered chemicals which they oversee to the ministry of Industry annually.

4/ The Ministry of Industry shall submit chemicals information report to the ministry on an annual basis.

**<u>PART THREE</u>**

**<u>RECORD KEEPING AND REPORTING</u>**

**7. <u>Record keeping</u>**

1/ Any person who is producing, importing, exporting, distributing, or using industrial chemicals shall keep the following information:

a) the type and amount of industrial chemicals produced, exported imported, distributed, and used;

b) the type and amount of industrial chemicals sold and distributed in the domestic market;

c) the type and amount of industrial chemicals that has been deteriorated as a result of improper management or prolonged storage;

መ) የኢንዱስትሪ ኬሚካሎቹ የተመረቱበት ሀገር፣ ያመረተው ድርጅት ስምና አድራሻ።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተመለከቱት መረጃዎች ቢያንስ ለአምስት ዓመታት ተይዘው መቆየት አለባቸው።

## ፰. ሪፖርት አቀራረብ

፩/ ማንኛውም የኢንዱስትሪ ኬሚካል አምራች፣ አስመጪ፣ ላኪ፣ አከፋፋይ ወይም ተጠቃሚ ያስመጣውን፣ የላከውን፣ ያመረተውን፣ ያከፋፈለውን፣ የተጠቀመውን ወይም ወደ ሦስተኛ ወገን ያስተላለፈውን የኬሚካል ዓይነትና መጠን በየዓመቱ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሪፖርት ማድረግ አለበት።

፪/ ማንኛውም ሰው ያመርተውን ወይም ያስመጣውን የኢንዱስትሪ ኬሚካል ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሪፖርት ሳያደርግ የኢንዱስትሪ ኬሚካል ንግድ ማከናወን አይችልም።

፫/ ማንኛውም የኢንዱስትሪ ኬሚካል አምራች፣ አስመጪ፣ ላኪ፣ አከፋፋይ ወይም ተጠቃሚ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች የመጠቀሚያ ጊዜ ከማለፉ ከአንድ ዓመት በፊት ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ማሳወቅ አለበት።

፬/ ማንኛውም የኢንዱስትሪ ኬሚካል አምራች፣ አስመጪ፣ ላኪ፣ አከፋፋይ ወይም ተጠቃሚ በይዞታው የሚገኙ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች በስርቆት ወይም በኃይል ወይም በሌላ መሰል ሁኔታዎች ወደ ሶስተኛ ወገን የተላለፉ ከሆነ በ፵፰ ሰዓት ውስጥ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው አካል ማሳወቅ አለበት።

d) the country, name and address where the industrial chemical has been produced.

2/ The information specified under sub-article (1) of this Article shall be maintained for a minimum of five years.

## 8. Reporting

1/ Any person who is producing, importing, exporting, distributing and using industrial chemicals shall, report annually to the Ministry of Industry, about the type and amount of industrial chemicals that are imported, exported, produced, distributed, used or transferred to a third party.

2/ No person shall engage in a business of industrial chemicals transaction without reporting to the Ministry of Industry the type and amount of industrial chemicals produced or imported.

3/ Any person who is producing, importing, exporting, distributing and using industrial chemicals shall report to the Ministry of Industry or competent authority one year before expiry date of the industrial chemicals.

4/ Any industrial chemical producer, importer, exporter, distributer and user, when dispossessed industrial chemical by a third party through theft or forcibly or by any other means shall inform the Ministry or the Competent Authority within 48 hours of loss of possession.

## ክፍል አራት
## የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ማሸግ፣ መለያ መስጠት፣ ማጓጓዝና ማከማቸት

**፱. ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት**

፩/ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ከ፲፰ ወር በታች የሆኑ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት የተከለከለ ነው።

፪/ ማንኛውም ሰው በአካባቢና በሰው ጤና ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመገምገም የሚያስችል የኬሚካል ባህሪይ እና የንጥረ ነገር ይዘት መረጃ በተጠየቀ ጊዜ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው አካል ማቅረብ ይኖርበታል።

፫/ ሚኒስቴሩ ልዩ ፈቃድ በመስጠት የመጠቀሚያ ጊዜያቸው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተጠቀሰው ጊዜ በታች የሆኑ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች እንዲገቡ ሊፈቅድ ይችላል።

፬/ "ልዩ ፈቃድ" ማለት ለአስቸኳይ የአደጋ ጊዜ ወይም ወረርሽኝን ለመከላከል ወይም ለመሰል ዓላማዎች ሲባል ለአስገቢው የሚሰጥ የጽሑፍ ማረጋገጫ ነው፤ ዝርዝሩ በሚወጣው ደንብ ይወሰናል።

**፲. ማሸግና መለያ መስጠት**

፩/ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባ፣ የሚያመርት፣ የሚያከማች ወይም የሚያጓጉዝ ማንኛውም ሰው በመያዣው ወይም በማሸጊያው ላይ፦

ሀ) የኬሚካሉ ምዝገባ ቁጥር፣ መጠሪያ ስም፣ መጠን እና የአገልግሎት ዓይነት፤

ለ) ኬሚካሉ የተመረተበት እና የአገልግሎት ማብቂያ ጊዜ፤

ሐ) የኬሚካሉ ባህሪይ እና የንጥረ ነገር ይዘት የሚያሳይ መረጃ፤ እና

መ) ኬሚካሉ የተመረተበት ሀገር፣ የአምራቹ ድርጅት ስም እና አድራሻ መረጃዎች የተለጠፉ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

## PART FOUR
## IMPORTATION, PACKING, LABELING, TRANSPORTING AND STORING OF INDUSTRIAL CHEMICAL

**9. Importation of Industrial Chemicals**

1/ The importation of industrial chemicals the shelf-life of which is below 18 months is prohibited.

2/ Any person, upon request by the Ministry or competent authority, shall submit characteristics and chemical composition of industrial chemicals to assess the impact of industrial chemicals on environment and human health.

3/ The Ministry may provide special permit for importation of industrial chemicals the shelf-life of which is below the period prescribed under sub-article (1) of this Article.

4/ "special permit" means a written approval for the importer in case of Emergency or control of epidemic or similar purpose; the detail shall be by regulation.

**10. Packing and labeling**

1/ Any person who produces, imports, stores or transports industrial chemicals shall be responsible to ensure that the following information chemicals are labeled on container and package:

a) Registration number, name, quantity and the use of industrial chemicals;

b) manufactured and expiry date of the industrial chemicals;

c) the characteristics and chemical composition of the industrial chemicals; and

d) the country of production, name and address of the industrial chemical producer.

፪/ ማንኛውም ሰው የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ማሸግ ወይም ዳግም ማሸግ የሚችለው መያዣያው፦

ሀ) አደጋ በማያደርስ ሁኔታ ኬሚካሉን ለማከማቸት፣ ለአያያዝ እና ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል፤ እና

ለ) በግልፅ ጎልቶ የሚታይ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ የተዘጋጀ እና በቀላሉ የማይለቅ የመለያ ምልክት ያለው ከሆነ፣

ብቻ ነው።

**፲፩. <u>የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ማጓጓዝ</u>**

የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን በማጓጓዝ ላይ የተሠማራ ማንኛውም ሰው ፦

፩/ ኬሚካሎች በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲(፩) የተገለፁ መረጃዎች በመያዣቸው ወይም በማሸጊያቸው ላይ የተለጠፈባቸው መሆኑን፤

፪/ለኢንዱስትሪ አገልግሎት የሚውሉ ኬሚካሎችን ከመንገደኞች፣ ከእንስሳት ወይም ከምግብና መድሀኒት ጋር በአንድ ላይ አለመጓጓዙን፤

፫/ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ለማጓጓዝ የሚጠቀምበት ተሽከርካሪ የድንገተኛ አደጋ መከላከያ መሳሪያዎችን ያሟላ መሆኑን፤ እና

፬/ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች በሚጫኑበት እና በሚራገፉበት ጊዜ የአደጋ ሥጋት የማያስከትሉ መሆኑን፤

ማረጋጥ አለበት።

**12. <u>የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ማከማቸት</u>**

1/ ማንኛውም የኢንዱስትሪ ኬሚካል ማከማቻ፦

ሀ) የሕንፃ ዲዛይኑ፣ ግንባታና አደረጃጀት በሰው፣ በእንስሳት እና በአካባቢ ላይ አደጋ እንዳያስከትል ለዚሁ ተግባር ተብሎ የተጠቀሰውን ደረጃ በሚያሟላ መልኩ የተገነባ መሆን አለበት፤

2/ Any person may pack or repack industrial chemicals, only if it is in a container which:

a) is safe for storage, handling and use; and

b) prominently displays a legible label in English or Amharic which and cannot easily be detached.

**11. <u>Transportation of Industrial Chemicals</u>**

Any person who is engaged in transportation of industrial chemicals shall ensure:

1/ that the chemicals are labeled on containers and packages in accordance with Article 10 (1) of this Proclamation;

2/ that the industrial chemicals are not being transported along with passengers, animals, or food and drugs;

3/ that any means of transportation of industrial chemical shall be outfitted with the emergency response equipments;

4/ that the loading and unloading of industrial chemicals do not cause risks.

**12. <u>Storage of Industrial Chemicals</u>**

1/ Any storage facility of industrial chemicals shall:

a) be built in such a way that the design, construction and arrangement of the building do not cause risks to human, animals and environment and comply with the standards set facility for this purpose;

ለ) የተበላሹ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ተለይተው የሚከማቹበት የተለየ ክፍል የተዘጋጀለት መሆን ይኖርበታል፤

ሐ) የኬሚካሎችን እና የመያዣቸውን ሁኔታ መደበኛ የሆነ የምልከታ ቁጥጥር ለማድረግ ተደራሽ የሆነ እና በመያዣቸው ላይ የደረሰን ጉዳትና ትክክለኛ ያልሆነ መለያን ለማስተካከል የሚያስችል ሥርዓት የተዘረጋለት መሆን ይኖርበታል።

፪/ የደረቅ ወደቦች እና ኤርፖርቶች ጊዜያዊ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ማቆያ ወይም ማከማቻ የሚሆን የተለየ ስፍራ ማዘጋጀት አለባቸው።

**፲፫. <u>የመተባበር ግዴታ</u>**

፩/ አግባብነት ያላቸው አካላት ኬሚካሎች በሰው እና በእንስሳት ጤና እንዲሁም በአካባቢ ደህንነት ላይ ጉዳት በማያሥከትል ሁኔታ እንዲያዙ፣ ጥቅም ላይ እንዲውሉ እና እንዲወገዱ በቅንጅት መስራት አለባቸው።

፪/ አግባብ ያላቸው አካላት የሚያሥተዳድሯቸው ኬሚካሎች የተመዘገቡ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

፫/ አግባብነት ያላቸው አካላት ሃላፊነት እና ሚና ዝርዝር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

**፲፬. <u>የክትትል እና የቁጥጥር ሃላፊነት</u>**

ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ተከትለው በሚወጡ ሕጎች መሠረት ኬሚካሎችን የተመለከቱ ተግባራትን በበላይነት የመከታተል፣ተፈፃሚነቱን የመቆጣጠር ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

b) have a separate compartment for storing of deteriorated and obsolete chemicals separately;

c) be accessible to carry out visual inspection of chemicals and its container on regular basis and put in place a procedure for dealing with any issues that may be identified such as damage to containers and illegible labels.

2/ Dry ports and airport shall arrange a separate temporary industrial chemicals storage compartments.

**13. <u>Collaborative responsibilities</u>**

1/ The Competent authority shall work in synergy to ensure chemicals are managed, used and disposed without causing damage on the human or animals health and to the environment.

2/ The entities which compromise the competent authority shall ensure all administered chemicals are registered.

3/ The detail responsibilities and roles of the competent authority shall be determined by regulation to be issued by the council of ministries.

**14. <u>Monitoring and Regulatory Responsibilities</u>**

In accordance with this proclamation and other laws enacted with pursuant of this proclamation the ministry shall have the authority to monitor and control enforcement of chemical related activities.

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፭. ቅጣት

ማንኛውም ሰው፦

፩/ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችን በሚቃረን ሁኔታ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች እንቅስቃሴ ላይ የተሳተፈ እንደሆነ፣ወይም

፪/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከሚኒስቴሩ ሳያገኝ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ያመረተ፣ ከውጭ ሀገር ያስገባ፣ የተጠቀመ ወይም ያከፋፈለ እንደሆነ፤ወይም

፫/ አግባብ ባለው የደረጃ አውጪ አካል የወጣውን የደረጃ መስፈርት የማያሟላ የኢንዱስትሪ ኬሚካል ያመረተ፣ ከውጭ ሀገር ያስገባ፣ የተጠቀመ ወይም ያከፋፈለ እንደሆነ፤ወይም

፬/ በዚህ አዋጅ የተጠቀሱትን መረጃዎች ወይም ሰነዶችን በሚመለከት ሆን ብሎ የሀሰት ማስረጃ ያቀረበ እንደሆነ፤ ወይም

፭/ ያልተመዘገቡ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎችን ያመረተ፣ ከውጭ ሀገር ያስገባ፣ የተጠቀመ፣ ወይም ያከፋፈለ እንደሆነ፤ ወይም

፮/ የአገልግሎት ጊዜ በማብቃቱ ወይም በመበላሸቱ ምክንያት ጥቅም ላይ የማይውል የኢንዱስትሪ ኬሚካል ለሚኒስቴ ሪፖርት ያላቀረበ እንደሆነ፤

ከሁለት ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና ከ፩፻ሺ ብር በማያንስ እና ፭፻ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

### ፲፮. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅን እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

## PART FIVE

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 15. Penalty

Whosoever:

1/ engages in transaction of industrial chemicals in a manner against the provisions of this Proclamation; or

2/ imports, produce, uses or distributed industrial chemical without having certificate of competence issued from the Ministry; or

3/ produces, imports, uses or distributes industrial chemical which does not meet the standards set by the relevant standard setting body; or

4/ intentionally provides false information or document for information requested pursuant to this Proclamation; or

5/ Produced, importd, used or distributed industrial chemicals; or

6/ fails to inform the Ministry or competent authority about chemicals that can no more of be use due to their expiration or deterioration;

shall be punished with rigorous imprisonment of not less than two year and not exceeding five years and with a fine not less than Birr 100,000 and not exceeding Birr 500,000.

### 16. Power to issue Regulations and Directive

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Ministry may issue directive for the implementation of this Proclamation and regulations issued under sub-article (1) of this Proclamation.

**፲፯. <u>ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>**

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም የአሰራር ልማድ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

**፲፰. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ መጋቢት ፳፯ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**17. <u>Inapplicable Laws</u>**

No law or practice shall, in so far as it is inconsistence with this Proclamation, be applicable with respect to matters covered under this Proclamation.

**18. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 5th day of April,2018.

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**